ቁጥር: ም/ሥ/ጉ/ጉ/00395/10
ቀን: 21/09//2010

- ለጉምሩክ ስነ ስርዓት አፈፃፀም የስራ ሂደት
- ለህግ ማስከበር የስራ ሂደት
- ለድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የስራ ሂደት
- ለቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ጉ/ስ/ስ/አ/ስራ ሂደት
- ለኢስተርን ኢንዱስትሪ ዞን ጉ/ስ/ስ/አ/ስራ ሂደት
- ለመንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመ/የተ/መ/ቡድን

- ከ፡ ጉምሩክ ጉዳዮች ም/ስራ አስኪያጅ
  አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ገ/እግዚአብሔር ገ/ፃድቅ
የጉምሩክ ጉዳዮች ም/ስራ አስኪያጅ
G/EGZIABHER G/TSADK
CUSTOMS AFFAIR DEPUTY MANAGER

የዋጋ ትመናና ታሪፍ ምደባ አሰራርና ፕሮግራም ልማት ዳይሬክቶሬት በደብዳቤ ቁጥር 4.3/281/10 ግንቦት 17/2010 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በጉምሩክ ታሪፍ ሁለተኛ መደብ "ሀ" ዝርዝር ውስጥ በተለያዩ የታሪፍ ቁጥሮች ላይ የኤሌክትሪክ ሲስተም አምራች ሲያስመጧቸው ተብሎ በማበረታቻው ተጠቃሚ እንዲሆኑ የተገለፀበት አገላለፅ አሻሚ ትርጉም በመሆኑና ለአፈፃፀም ክፍተት ያለው በመሆኑ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር ማብራሪያ እንዲሰጥበት ተጠይቆ በቁጥር ማአ..30/47/15 በ10/09/2010 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ማብራሪያ የላከ መሆኑን ያሳወቁን ስለሆነ በማብራሪያ መሰረት ተግባራዊ እንዲሆን እያሳሰብኩ የተላከውን 4 ገጽ ደብዳቤ በአባሪነት አያይዘን ልከንላችኋል።

ከሰላምታ ጋር

ግልባጭ፣
- ለሥራ አስኪያጅ ጽ/ቤት
- ለም/ስራ አስኪያጅ /ህግ ማስከበር ዘርፍ/
  አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት
A.A Kaliti Customs Branch Office
የሪከርድ ሥራ አመራር ቡድን
የደረሰበት ቀን 18/9/10
የተቀባይ ስም
ፊርማ
የተመራለት ሥራ ሂደት/ቡድን ለሞ/አኪ[illegible]
የማህደር ቁጥር [illegible]
የተመለሰበት ቀን
መለያ ቁጥር 1

- ለኤርፖርት ጉ/ቅ/ፅ/ቤት
- ለቃሊቲ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ፅ/ቤት
- ለሐዋሳ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት
- ለመቀሌ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት
- ለሚሌ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ጉ/ቅ/ፅ/ቤት

<u>በያሉበት</u>

